አንድ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፣ አንድ ፡ ኢትዮጵያ ፣ አንድ ፡ የባሕር ፡ ወደብ ፣ አንድ ፡ በፍቅር ፡ ተሣሥሮ ፡ ለነፃነቱ ፡ ታጋይ ፡ ሕዝብ ፣ አንድ ፡ ሕዝባዊ ፡ አገር ፡ አስተዳደር ፣ አንድ ፡ የተረጋጋ ፡ ምጣኔ ፡ ሀብታዊ ፡ ልማት ፣ አንድ ፡ ለማስተዳደር ፡ ብቁነቱን ፡ አስመስክሮ ፡ በሕዝብ ፡ ተወዶ ፡ የተመረጠ ፡ መሪ ፣ አንድ ፡ በውኅደቱ ፡ የፀና ፡ ድርጅትና ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ከሰላምና ፡ ጤና ፡ ጋራ ፡ ያስፈልጉናል።

## “አገሬን ፡ ያለ ፡ ወገሬን” ፡ እንደሚሉት ፤

ወገሬ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለማታውቁ ፡- በቆሳ ፡ ተዘርቶ ፡ የሚመረትና ፡ መረር ፡ ያለ ፡ ቃና ፡ ያለው ፡ የዘንጋዳ ፡ ዘር ፡ ነው ። ከአጠቃቀሙም ፡ አንዱ ፡ አሻሮ ፡ ለመሆን ፡ ተቆልቶ ፡ ለጠላ ፡ ነው ። ጠላነቱ ፡ የሚያመረቃና ፡ ካልተጠነቀቁበትም ፡ ቶሎ ፡ እራስን ፡ ወግቶ ፡ ያሳምማል ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ አበው ፡ ለውዲቱ ፡ እናት ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገሩ ፡ የሚታገል ፡ ቆራጥና ፡ መራርነት ፡ ስለሚጠይቅ ፡ ለወገሬ ፡ የተጻፈለት ። ወጣቱ ፡ ትውልድ ፡ ግራ ፡ ተጋብቶ ፡ የቆራጥነቱን ፣ የባሕሉን ፣ የታሪኩን ፣ የቋንቋውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ምግባር ፣ ለእናት ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገሩ ፡ ፍቅሩንና ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ አከባበሩን ፡ አላልቶ ፡ ወለም ፡ ዘለም ፡ አብዝቷል ። እየ ተባለ ፡ በጭንቀት ፡ ይነገራል ። ማን ፡ አስተማረውና! ፡ ወይም ፡ ወለም ፡ ዘለምተኝነቱንና ፡ አፉ ፡ እንዳመጣ ፡ ደፍሮ ፡ መናገሩን ፡ ከማን ፡ ተማረው? ብለን ፡ ጠይቀን ፡ እናውቃለን? እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ባሕል ፡ ተበክሎ ፡ ከማለት ፡ በስተቀር ፡ ስሕተቱን ፡ እንዲያርም ፡ አልተጣረም ። እናም ፡ የዜግነት ፡ ግዴታችን ፡ ስለሆነ ፡ ልናሥብበት ፡ ይገባል ። እንደዚህ ፡ እንድናሥብ ፡ ያስገደዱንን ፡ የእናት ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሕዝቧ ፡ በተሻለ ፡ ሁኔታ ፡ የሚዳብሩበትን ፡ በሚፈልጉና ፡ የዐዋቂ ፡ አጥፊ ፡ እንቅፋት ፡ በሆኑባቸው ፡ ያነበብነውን ፡ አጥንተን ፡ ካመዛዘንና ፡ ካሰላሰልን ፡ በኋላ ፡ ነው ። የመማር ፡ ትርጉሙ ፡ ክፉውንና ፡ ደጉን ፡ በመለየት ፡ ለመመራመር ፡ ነው ። ከእኔ ፡ በላይ ፡ ምሁር ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ መድፈር ፡ አይገባም ። ይኸን ፡ ካልን ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ቅንጅት ፡ መከፋፈል ፡ ሥር ፡ ሰደድ ፡ ምክንያቱን ፡ ዐውቀው ፡ ቃለ ፡ መጠይቅ ፡ ተደርጎላቸው ፡ ስለመለሱት ፡ ምሁር ፡ እንሆ!

የተከበሩት ፡ የትምህርተ ፡ ምድር ፡ መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደማርያም ፡ “ኑዛዜ” ፣ በቅንጅት ፡ መሥራችና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ተወካይን ፡ መሪ ፡ 1*“ኀላፊነት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አለመረዳቱን ፡ ነው ፡ የሚያሳየኝ” ። ካሉ ፡ በኋላ ፣ በብርሃኑ ፡ ነጋና ፡ በተከበሩት ፡ የቅንጅት ፡ መሪ ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ 2*“...... መካከል ፡ ያለው ፡ ቅራኔ ፡ የዓላማ ፡ ልዩነት ፡ ሳይሆን ፡ የሥልጣን ፡ ጥመኝነት ፡

ነው ። ወይዘሮ ፡ ብርቱካን ፡ ሚዴቅሳ ፡ ጥሩ ፡ አገር ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ሊወጣት ፡ የም
ትችል ፡ ናትና ፡ እርዷት ። ከዚህ ፡ አጣብቂኝ ፡ እንዴት ፡ እንደምትወጣ ፡ ግን ፡ መ
በርታት ፡ አለባት ” ። ብለው ፡ ትእዛዝ ፡ አስተላለፉ ። በሕገ ፡ ወጥነት ፡ ከሌሎች ፡
ጋራ ፡ ሆና ፡ አሳድማ ፡ ቅንጅትን ፡ ለመከፋፈል ፡ የምትሯሯጥበት ፡ መሆኗን ፡ ግን ፡
ተይ ፡ ብለው ፡ ሊመክሯት ፡ አልፈለጉም ። ቤት ፡ ዘግተው ፡ በጨለማ ፡ አልቃሾች
ና ፡ የባለ ፡ ሃምሣ ፡ አምልኮ ፡ ተከታይ ፡ በመሆኗም ፡ ለሕዝብ ፡ ምንም ፡ ደንታ ፡ እ
ንደሌላት ፡ ማስረጃ ፡ አለን ። የሕዝብ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ለመሆ ፡ ብቃት ፡ አላት ፡ ለሚ
ሏት ፡ ሴት ፡ ይኸን ፡ መመልከት ፡ እንዴት ፡ ይሳናታል? ። ማስረጃችን ፡ ያልነው
ም ፦ 3*የውጭ ፡ ዜጋ ፡ ባለ ፡ ሃምሣ ፡ አምልኮተኞች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዜጎቿን ፡
በመሬት ፡ አንጋለው ፡ የቀኝና ፡ ግራ ፡ እጅና ፡ እግሮቻቸውን ፡ እረግጠው ፡ ይዘው ፡
ሲያሰቃዩዋቸው ፡ አንድም ፡ የተቃውሞ ፡ ቃል ፡ አልወጣትም ። የሰቆቃውን ፡ ተንቀሳ
ቃሽ ፡ ንሺም ፡ ለአገርና ፡ ወገን ፡ ተቆርቋሪው ፡ ጉበዝ ፡ የተከበሩት ፡ አቶ ፡ ጌታቸ
ው ፡ ረዳ ፡ አስተታልፈውት ፡ ዓይተነዋል ። ቆራጡ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወኪል
ና ፡ መሪ ፡ ክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውልም ፡ በመረጃ ፡ አረጋግጠው ፡ አምስ
ቱን ፡ አድመኞች ፡ አግደው ፡ የላዕላይ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ እንዲወስንበት ፡ አሳሰቡ ።
ይህ ፡ በሚገባ ፡ ታሥቦበትና ፡ ዘግየት ፡ ብሎ ፡ የመጣ ፡ ውሳኔ ፡ በእኛ ፡ በኩል ፡ ዕል
ልታ ፡ ሲሆን ፣ በእነሱ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ዋይ ፡ ዋይታ ፡ ሆኖ ፡ እየተመለከትን ፡
ነው ። በዚህም ፡ ሁኔታ ፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ እየጠበቁ ፡ በመናደፍ ፡ ከወጣትነታቸው ፡
ጀምሮ ፡ የታወቁት ፡ የአሁኑ ፡ ሽማግሌ ፡ መምህር ፡ መስፍን ፡ 4*“የሕግ ፡ ሴት ፡ ስለ
ሆነች ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ አሥባ ፡ ለመሥራት ፡ ችሎታው ፡ አላት” ፡ ብለው ፡ ከዳኙት ፡
በስተኋላ ፡ ቆመውና ፡ መኪናቸውንም ፡ ለአድመኞች ፡ መጓጓዣ ፡ ሲያውሱ ፡ ቆይተ
ው ፡ በሕገ ፡ ወጥነት ፡ ከትግሬ ፡ ወያኔ ፡ አምባገነን ፡ የሕዝብን ፡ ነፃነትና ፡ ሕይወት ፡
አውዳሚ ፡ ጋራ ፡ ለመተባበር ፡ ዝግጅት ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። የወሰዱት ፡
እርምጃ ፡ “እኔ ፡ ከሞትኩ ፡ ሰርዶ ፡ አይብቀል” እንደሚሉት ፡ ካላሠቡ ፡ በስተቀር ፡
እጅግ ፡ በጣም ፡ አደገኛ ፡ ነው ። ተተኪው ፡ ወጣት ፡ ትውልድ ፡ በአሰልስሎው ፡ ገዳ
ይ ፡ በሽታና ፡ በትግሬ ፡ ወያኔ ፡ አምባገነን ፡ አረመኔ ፡ ነብሰ ፡ ገዳዮች፡ እየተጨረሰ ፡
ባለበት ፡ ወቅት ፡ ለማዳን ፡ ውክልና ፡ ቆመው ፡ በመሟገት ፡ ፈንታ ፡ ለእልቂቱ ፡ ተ
ባባሪ ፡ መሆን ፡ ጤነኛ ፡ የሆነ ፡ አስተሣሠብ ፡ አላቸው ፡ ለማለት ፡ ያዳግታል ። ስለ
ሆነም ፡ ከውጭና ፡ አገር ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕዝብ ፡ የወሰዱትን ፡ ሕገ-
ወጥ ፡ እርምጃ ፡ ተረባርቦ ፡ በሕዝብ ፡ ኃይል ፡ ሊያግዳቸው ፡ ይገባል ።

ክቡራትና ፡ ክቡራን ፡ ወገኖቻችን ፡ ሆይ!

ግዜው ፡ እየበረረ ፡ የትግሬ ፡ ወያኔ ፡ አምባገነን ፡ ነብሰ ፡ ገዳይ ፡ አረመኔ ፡ ከ
ደደቢት ፡ ጫካ ፡ ወጥቶ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከገባ ፡ ዓሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሊያልፈ
ው ፡ ነው ። ያን ፡ ግዜ ፡ ለንደን ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ለዜጋው ፡ ሕዝብ ፡ አስተዳዳሪ
ነት ፡ ድርድር ፡ የተከበሩት ፡ አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ዲንቃ ፡ በብቁነት ፡ ሲሟገቱ ፡ አንሰማ
ህም ፡ ተባሉ ። ከዚያም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋው ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ኸርማን ፡ ኮኸን ፡
አጋርነት ፡ ያለ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ፍላጐት ፡ ሥልጣን ፡ ለወያኔ ፡ በግዜያዊነት ፡ ተ
ሰጠ ። አዲስ ፡ አበባም ፡ ወያኔ ፡ ሲገባ ፡ የመጀመሪያ ፡ ሰለባ ፡ እንድትሆን ፡ የተፈረደ
ባት ፡ የጥይት ፡ ምርት ፡ ማምረቻችን ፡ ነበረች ። በእሳት ፡ አጋይዋት ። የአገራችን ፡
ተግባረ ፡ ዕድና ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ መማሪያዎች ፡ በየትምህርት ፡ ቤቶች ፡ እየተነቀሉ ፡
ወደ ፡ አሥመራና ፡ መቀሌ ፡ ተጫኑ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ መምህር ፡ ኤፍሬም ፡ ይሥ

ሐቅን ፡ ጥሎብን [5*]“በክቡር ፡ አቶ ፡ መለስ ፡ ዜናዊ ፡ መሪነት ፡ የሀገር ፡ ሽማግሌና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መወያየት ፣ ሰላምን ፡ መፍጠር ፡ ነው ፡ የሚሻለው ። ብለው ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ መሪነት ፡ በማሳየታቸው ፡ በውነቱ ፡ ሁላችንም ፡ ማመስገን ፡ አለብን ። (ብርቱካንን ፡ ነው) ። እኒህ ፡ ወንድሞቻችን ፣ እህቶቻችን ፣ ያገር ፡ ባሕል ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ያገር ፡ ሽማግሌ ፡ ማክበር ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ያገር ፡ ሽማግሌ ፡ ምክር ፡ ሰምተን ፡ ከመንግሥት ፡ ጋር ፡ እንዋደድ ። እንፋቀር ። እንታረቅ ። አብረን ፡ እንሥራ ። ይህች ፡ ትልቅ ፡ አገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡ የሰጣት ። ጥሩ ፡ መሬት የሰጣት ። ጥሩ ፡ የተማሩ ፡ የጥንት ፡ ሰዎች ፡ የሰጣት ። አሁን ፡ ዛሬ ፡ እኛ ፡ እዚህ ፡ ያለነው ፡ ይኸንን ፡ ትልቅ ፡ በእጃችን ፡ ያለውን ፡ ትልቁን ፡ ወርቅ ፡ ብናበላሸው ፡ ታሪክ ፡ ይፈርድብናል” ። ብለው ፡ እየሰበኩ ፡ እለቁ ፡ እንደማለት ፡ [6*]“ኑሩ” ይሉናል ። አባባላቸውን ፡ በሚገባ ፡ ላመዛዘነው ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ አረመኔ ፡ ቢሆኑ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እልቂትና ፡ የሀገራችን ፡ መቆራረስ ፡ ሳይታሰባቸው ፡ የሚወተውቱ ፡ ያሰኛል ። ስለ ፡ ገባሩ ፡ ሕዝብ ፡ አለማውራታቸውስ ፡ አያበሳጫችሁም? መምህሩን ፡ ዛሬ ፡ ሳይሆን ፡ ስድስተኛና ፡ ሰባተኛ ፡ ክፍል ፡ እያለን ፡ የብሔራዊ ፡ ፊደል ፡ ሠራዊት ፡ ድርጅት ፡ ኀላፊ ፡ ሆነው ፡ እናውቃቸዋለን ። እኛ ፡ በክረምት ፡ ጭቃ ፡ እየማቀቅን ፡ በነፃ ፡ ስናስተምር ፡ መምህሩ ፡ ዓለማትን ፡ ለብሔራዊ ፡ ፊደል ፡ ሠራዊት ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ላቋቁም ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ገንዘብ ፡ አከማችተው ፡ በተግባር ፡ ሳናየው ፡ ቀርተናል ። ታዲያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በሥውር ፡ ይሠሩት ፡ የነበረው ፡ ወደ ፡ መጋለጡ ፡ ሲቃረብ ፡ ዘዴያቸውን ፡ ቀይረው ፡ የሽማግሌዎች ፡ አስተባባሪ ፡ በመሆን ፡ አስታርቃለሁ ፡ በማለት ፡ እያታለሉ ፡ ቅንጅትን ፡ ይከፋፍላሉ ። እንግዲህ ፡ ወገኖቻችንን ፡ አደራ ፡ የምንለው ፡ ለማንም ፡ ቅጥረኛ ፡ ሰላይ ፡ ሳናጎበድድ ፡ አገርና ፡ ወገናችንን ፡ ለማዳን ፡ በሐቀኝነትና ፡ ቆራጥነት ፡ ከሚታገለው ፡ ቅንጅት ፡ ጋራ ፡ ትብብር ፡ እንዲኖረን ፡ ነው ። በውጭ ፡ ፎሪዎችን ፡ ለማመስገን ፡ የመጡትን ፡ ዋሽንግተን ፡ ዲ ፡ ሲ ፡ ላይ ፡ ሰብስበው ፡ ገለልተኛ ፡ የተባሉትን ፡ አሰባሳቢዎች ፡ ጭምር ፡ ካነጋገሯቸው ፡ በኋላ ፡ ሁኔታው ፡ የተባባሰ ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብም ፡ ይኖርብናል ። አሁንም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ የነበሩትንና ፡ ፈርመው ፡ የወጡትን ፡ አየሰበኩ ፡ እነ ፡ መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደማርያም ፡ በሕገ ፡ ወጥነት ፡ በሕዝብ ፡ ሳይመረጡ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ገብተዋል ። ወይዘሮ ፡ ብርቱካንም ፡ የዳኝት ፡ ሕገ ፡ ወጢትነት ፡ መርጣ ፡ ያለ ፡ ቅንጅት ፡ ሕገ ፡ ደንብ ፡ እራሷን ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፣ አቶ ፡ ተመስገን ፡ ዘውዴን ፡ ምክትል ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ አድርጋ ፡ ሹማለች ። የሕዝባዊ ፡ መንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እንመሠርታለን ፡ ማለት ፡ እንደዚህ ፡ የሕዝብን ፡ መብት ፡ ቀምቶ ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ እንወቅልህ ፡ ለማለት ፡ ነወይ? ወይዘሮ ፡ ብርቱካን ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሞኑን ፡ የወሰደችው ፡ የቅንጅትን ፡ መሪ ፡ ስም ፡ ማጥፋት ፡ እርምጃ ፡ [7*]“......ኢንጅነር ኃይሉ ሻውልን ሰዎች ፡ ይጠሏቸዋል ።ሆኖም አሁን የቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ፓርቲ ፕሬዝዳንት እሳቸው ናቸው!”[8*]“የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ” በሚል ርዕስ ወረቀትም በመበተን [8*]“........ ወቅቱ የግርግር በመሆኑ በፕሮፌሰር አሥራትና በሌሎች ሰዎች ላይ የፈጸሙት በደል ተድበስብሶ መጥፎ ተግባርዎ በቅንጅት ታድሶ በሊቀ መንበርነት ሹመት ......ይህ ሁሉ እንግልት ፤ ሞት ፤ እሥራትና ስደት የተከሰተው እርስዎ በሰጡት አመራር ምክንያት መሆኑአጠያያቂ አይደለም” ። የተባለውም ፡ አገርና ፡ ወገንን ፡ አስከፊ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሊጥል ፡ የሚችል ፡ ስለሆነ ፡ አማካሪዋ ፡ መምህር ፡ መስፍንን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የያዘ ፡ አካሄድ ፡ እንዲመርጡ ፡ አደራ ፡ እንላለን ። ስለ ፡ ተከበሩት ፡ ሐኪም ፡ ዓሥራት ፡ ወልደየስ ፡ ተጠያቂው ፡ መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደማርያምን ፡ ቢደረግ ፡ የተሻለ ፡ ይመስለና

ል ። ምክንያቱም ፡ አሳጥተው ፡ በትግሬ ፡ ወያኔ ፡ አስጠምደው ፡ ለሞት ፡ የበቁበትን ፡ እንደሚከተለው ፡ እንገልጻለን ፦

የትግሬ ፡ ወያኔ ፡ አምባገነን ፡ ነብሰ ፡ ገዳይ ፡ መንግሥት ፡ ተብየውን ፡ የምን ቃወመው ፡ የዘረኛነት ፡ መርዝ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ስለበተነ ፡ ያ ፡ እንዳይበክለ ን ፡ ነው ። ወደር ፡ የለሹን ፡ የቀዶ ፡ ጥገናና ፡ በዓለማት ፡ የታወቁት ፡ ንጹሕ ፡ ኢት ዮጵያዊ ፡ የተከበሩትን ፡ ሐኪም ፡ ዓሥራት ፡ ወልደየስ ፡ ያለ ፡ ስማቸው ፡ ስም ፡ በመ ስጠት ፡ የጫሩት ፡ ለመሞት ፡ አበቃቸው ። ክቡር ፡ ሐኪም ፡ ዓሥራት ፡ ወልደየስ ፡ በሥነ ፡ መንግሥቱ ፡ እንቅስቃሴ ፡ የመግባት ፡ ሐሣብ ፡ አልነበራቸውም ። እንዲገ ቡ ፡ የገፋፉቸው ፡ ሰቆቃ ፡ በአርባ ፡ ጉጉ ፡ ከነ ፡ ነብሳቸው ፡ የተቀበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ካዩ ፡ በኋላ ፡ ነበረ ። መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደማርያም ፡ ግን ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ላይ ፡ ክቡር ፡ ሐኪም ፡ ዓሥራት ፡ ወልደየስ ፡ ሰዎችን ፡ ሰብስበው ፡ ሲያናግሩ ፡ ሰም ተው ፡ “በጠረጴዛ ፡ ዙሪያ ፡ መወያየት ፡ እንጂ ፡ ይኽ ፡ ዓይነት ፡ ቅስቀሳ ፡ አያስፈል ግም” ፡ ሲሏቸው ፡ “እሱን ፡ አንተ ፡ አድርገው” ፡ ባሏቸው ፡ መሠረት ፡ አኩርፈው ፡ ጦርነት ፡ ሊያስከፍት ፡ ነው ፡ አሰኝተው ፡ ባቀጣጠሉት ፡ ክቡር ፡ ዓሥራትም ፡ ለሚወ ዷት ፡ ኢትዮጵያና ፡ ወገናቸው ፡ ነብሳቸውን ፡ ይማርና ፡ መሥዋዕት ፡ ሆኑ ።

ስለ ፡ መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ጠንከር ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ መስጠት ፡ የፈለግንበት ፡ ምክንያት ፡ የሚያቀርቧቸው ፡ ሐሣቦች ፡ ለቀስተ ፡ ደመናዎ ቹ ፡ እንደሚያደሉ ፡ ስለተሰማንና ፡ የከፋ ፡ ልምድ ፡ ስላላቸው ፡ ነው ። ግዜ ፡ የሚያ ጓትት ፡ ሁኔታ ፡ የመፍጠር ፡ ነገር ፡ አጫሪ ፡ ለመሆናቸው ፡ ያደረግነውን ፡ ጥናት ፡ እናካፍላችሁ ፦

፩ኛ ፤ “[9]*ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የመርማሪ ኮሚሽን ሊቀ መንበር ፣ ዶክተር በረከተአብ ሀብተሥላሴ ደግሞ ምክትል ሊቀ መንበር ነበሩ ። ሁለቱም በደርግ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ >ተጠርተው ስለሥራቸው ፡ መጓተት ያስረዱ< ተባለ ። ሁለቱም ቀረቡ ። >ምንድነው ችግራችሁ? ሕዝቡ በኛ ላይ ግፊት እያደረገ ነው ። ለምንድ ነው ሥራችሁን የማታፋጥኑት?> ተብለው ተጠየቁ ። እነሱም መልስ ሲሰጡ >ይሄ ሕገ መንግሥት ወረቀት ነው ። ጠመንጃው ያለው በጃችሁ ነው ። ስለዚህ እኛን ይህ ነው ብሎ ከመውቀስ ፣ ጊዜ የሚጓተት ከሆነ ከዚህ በላይ ልንል የምንችለው ነገር የለም< የሚል አስተያየት ሰጡ” ።

፪ኛ ፤ በ፲፱፻፷፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወሎ ፡ ስለድረሰው ፡ ረኀብ ፡ አጋልጠ ው ፡ የዘውድ ፡ አስተዳደሩ ፡ እንዲለወጥ ፡ በመደረጉ ፡ “የኢትዮጵያ ፡ ዮሴፍ” ፡ በሚ ል ፡ ቅጽል ፡ ስም ፡ እንደተጻፈላቸውና ፡ በአንጻሩም ፡ አስቸጋሪ ፡ ሰው ፡ እንደሆኑ ፡ ታትቷል ። [10]*“ከመስፍን ጋራ የብዙ ዘመን ጓደኝነት ሲኖረን ፤ .......እስከ ዛሬ ድረ ስ የየት አገር ሰው እንደሆነ አልነገረኝም ። ወንድም ፤ እኅት ፤ አጐት ፤ አክስት ፤ ወይም ሌላ የሥጋ ዘመድ ፡ ይኑረው አይኑረው አላውቅም ። እናት አባቱ በልጅነቱ እንደሞቱ እንዳጋጣሚ አንድ ቀን አውርቶኛል ።.......በኢትዮጵያ ጉዳይ መስፍን ፊት ለፊት ያለ ይሉኝታ ያለ ፍርሃት ስለሚናገርና ስለሚጽፍ የሚያደንቁት ብቻ ሳይሆኑ የሚቀየሙትም አይጠፉ ። እኔ እንደሚመስለኝ ኢትዮጵያን እንደ ቤቱ ፤ ሕዝቧን እንደ ቤተ ሰቡ ቆጥሮ ነው ። .......በ፲፱፻፶፪ ዓመተ ምሕረት ትግሬ ላይ ረኀብ ሰው መቱን መዘለስ ደርሶ ነበር ። ለጠቅላይ ግዛቱ ሕዝብ እርዳታ በቅድሚያ የደረሰላቸው መስፍን ነው ። ከሸዋ እህል ያላቸው ሀብታሞች እየፈለገ በነፃ እንዲሰ ጡ አስረድቶ የሰጡትን ወስዶ አከፋፈለ ። አልበቃውም ፤ ብዙ ሰውም አለቀ ። መስ ፍን ግን ስንቁን ሳይቀር ሰጥቶ አዲስ አበባ ተመልሶ የገባው ጠኔ እያግተረተረው

በብዙ ማቃሰት ነው” ።
ደራሲውን ፡ ስለምናውቃቸው ፡ በታላቅ ፡ አክብሮት ፡ ለምናቀርበው ፡ አስተያ
የት ፡ ቅር ፡ እንዳይሰኙ ፡ አስቀድመን ፡ ይቅርታ ፡ እንጠይቃለን ። ታዲያ ፡ ይኸን ፡
የመሰለ ፡ አመለካከት ፡ ያላቸው ፡ መምህር ፡ መስፍን ፡ እንዴት ፡ ሌሎች ፡ አገርና ፡
ወገንን ፡ ለማዳን ፡ ሲነሱ ፡ እየተናደፉ ፡ እንቅፋት ፡ ይሆናሉ? የሸዋ ፡ አማራ ፡ እያለ
ስ ፡ የትግሬ ፡ ወያኔ ፡ ሕዝቡን ፡ በሚዘልፍበትና ፡ በሚገድልበት ፡ ወቅት ፡ ለትግሬ ፡
ረኀብተኛ ፡ ሸዋ ፡ ስላደረገው ፡ በጐ ፡ እርዳታ ፡ ገልጸው ፡ ለምን ፡ ጠንከር ፡ ብለው ፡
አልተቃወሙም? እናትና ፡ አባት ፡ ሆና ፡ ላሳደገች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወረታ ፡ ልጆቿን ፡
ወይም ፡ ወንድምና ፡ እህቶቹን ፡ በማስገደል ፡ ለሚረካ ፡ ምሁር ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይ
በጃል ፡ ትላላችሁ? ግብር ፡ ከፍሎና ፡ አስተምሮ ፡ ያሳደገን ፡ ሕዝብ ፡ ውለታ ፡ ለመ
ክፈል ፡ የታቀቡት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ዓይነ ፡ ኀሊና ፡ ቢኖራቸው ፡ ነው? ለዕድሜ ፡
ልክ ፡ ጭካኔ ፡ የተዳረጉት? ከሞት ፡ የተረፉና ፡ የተናዘዙ ፡ ሰው ፡ ንሥሐ ፡ ገብተው ፡
መጽዳትንና ፡ የሚች ፡ ሕዝብን ፡ ወገን ፡ ይቅርታ ፡ መጠየቅን ፡ እንዴት ፡ አይታሰባ
ቸውም? ለሀገርና ፡ ወገን ፡ ትግል ፡ ያለ ፡ ኅብረት ፡ እንደማይሳካና ፡ በኅብረት ፡ ጸሎ
ትም ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ በባሕላችን ፡ ተመስክሮ ፡ ሳለ ፤ አብረው ፡ ታጋይ ፡ ገደኞ
ችን ፡ እያስገደሉ ፡ አድነኝ ፡ ብለው ፡ መጸለያቸው ፡ እንደ ፡ በላየ ፡ ሰብ ፡ ጨካኝ ፡ አ
ያስብላቸውም ፡ ወይ? [11*]“ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ እምሕዝብ ውፁአን
እምፅድቅ” ። “አምላክ ሆይ! ከእውነት ከታቀቡና ከራቁ ሰዎች ጋር ተከራክረህ አድነ
ኝ” ። ሌሎች ፡ እኮ ፡ “ፍታሕ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ ወተበቀል ፡ በቀልነ ፡ እምሕዝብ ፡
ውፁአን ፡ እምፅድቅ” ። “አምላክ ፡ ሆይ! ከእውነት ፡ ከታቀቡና ፡ ከራቁ ፡ ሰዎች ፡
ጋር ፡ ተከራክረህ ፡ አድነን” ። በማለት ፡ እየታገሉ ፡ ነው። በሁለት ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡
በኢትዮጵያ ፡ ጸሎት ፣ በክቡር ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ ቆራጥነትና ፡ ጀግንነት ፡ ቅንጅት ፡
ተመሠረተ ። ለመጀመሪያም ፡ ግዜ ፡ በሕዝባዊ ፡ ምርጫ ፡ አሸንፎ ፡ የሕዝብ ፡ ኃይሉ
ን ፡ መሠረት ፡ ሲጥል ፡ ማበረታታት ፡ ሲገባቸው ፡ ለምን? ለአፍራሾች ፡ ምቹ ፡ እን
ዲሆን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ከሚገድል ፡ ጋራ ፡ ለሰላም ፡ ትግል ፡ በመፋለም ፡
ፈንታ ፣ ሊያስወግደው ፡ የሚሟሟተውን ፡ ይቃወማሉ? አሁንስ ፡ ወይዘሮ ፡ ብርቱካን
ን ፡ በተመለከተ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ መብት ፡ በሚገፍና ፡ በሚከፋፍልም ፡ ሐሣ
ብ ፡ ስትመራ ፡ መካሯ ፡ መሆናቸው ፡ ምን ፡ ይባላል? በቀስተ ፡ ደመና ፡ ድርጅታቸ
ው ፡ ሲጀመር ፡ ጀምረው ፡ የነበሩትና ፡ በኢሰመጉ ፡ አብረዋቸው ፡ እየታገሉ ፡ ያሉ
ት ፡ ብቁዋ ፡ ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ ንግሥት ፡ ገብረ ፡ ሕይወትን ፡ ገለል ፡ አድርገው ፡
በኋላ ፡ ኋሮ ፡ በግርግር ፡ የገባችውን ፡ የማማከር ፡ ዓላማ ፡ ፍርደ ፡ ገምድልና ፡ ከቅን
ጅት ፡ ሕገ ፡ ደንብ ፡ ውጭነትን ፡ አያስከትልም ፡ ወይ? ዘረኛስ ፡ አያሰኛቸውም ፡
ወይ? እሥር ፡ ቤት ፡ በነበሩበት ፡ ወቅት ፡ አያሌ ፡ ታጋይ ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ። እነሱን
ስ ፡ ለሕዝብ ፡ ማስተዋወቅን ፡ እንዴት ፡ አጡት? ሴትና ፡ ወንድ ፣ ወጣትና ፡ ሽማግ
ሌ ፡ ሳይባል ፡ የሀገርና ፡ ዜጋዎቿን ፡ ትግል ፡ ለማካሄድ ፡ እንጅ ፡ ወገን ፡ እየተለየ ፡
በደባ ፡ ለመታገልና ፡ ለሥልጣን ፡ ሽሚያ ፡ ነበረ ፡ ወይ? የሴቶች ፡ ማኅበርና ፡ እነ ፡
ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ ንግሥት ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ ሴቶች ፡ መቋቋም ፡ ሲያስተባ
ብሩ ፣ እባካችሁ ፡ ተሳትፎ ፡ ያስፈልጋልና ፡ ተሳተፉ ፡ ሲሉ ፡ እንሰማለን። የወይዘሮ ፡
ብርቱካንን ፡ ሐሣብ ፡ ይኸን ፡ በተመለከተ ፡ ማወቅ ፡ እንፈልጋለንና ፡ ሕዝብ ፡ እንዲ
ጠይቃት ፡ እናሳስባለን። ለግዜውም ፡ ስጋታችን ፡ በደርግ ፡ ዘመን ፡ ስድሳ ፡ ክቡራን ፡
ቁልፍ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ልጆች ፡ ያለ ፡ ፍትሕ ፡ ለመገደል ፡ ፍንጭ ፡ የሰጠ ፣ ለትግራ
ይ ፡ ወያኔው ፡ አምባገነን ፡ አረመኔ ፡ አሳጥቶ ፡ ለክቡር ፡ ሐኪም ፡ ዓሥራት ፡ ወልደየ

ሱስ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ የሆነን ፡ ዛሬስ ፡ ማንን ፡ አጥምዶ ፡ ይመስላችኋል? በኋላ ፡ ወይ ፡ ጉድ! ማለት ፡ አይጠቅምምና ፡ አሉን ፡ የምንላቸውን ፡ የቁርጥ ፡ ቀን ፡ ጀግናዎች ፡ እንከላከልላቸው ። እንጩህላቸው ። አቤት ፡ እንበልላቸው ። በዓለማት ፡ ፊት ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ ከማድረግ ፡ አንቆጠብ ።

ስለዚህ ፡ ወገኖቻችን ፡ ሆይ!

አለቀ ፡ ስንለው ፡ ተጀመረ ፡ እየሆነ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሕዝቧ ፡ እንዳያፍልን ፡ እንቅፋት ፡ የሚሆኑትን ፡ እየለየን ፡ በሰላም ፡ እንታገል ። እንደ ፡ ወገሬዋም ፡ መራር ፡ ሆነን ፡ እንድንነሣ ፡ ልቦናውን ፡ ይስጠን ። እነሱ ፡ የሚያወሩት ፡ ስለ ፡ ሥልጣን ፣ በለመኑት ፡ ገንዘብ ፡ ድኀነው ፡ ወገናቸውን ፡ በመደለል ፡ ድጋፍ ፡ ማግኜትና ፡ ክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውልን ፡ ስለ ፡ ማስወገድ ፡ ነው ። ክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ ደግሞ ፡ በየቦታው ፡ እየዞሩ ፡ አደራ ፡ እያሉ ፡ የሚናገሩት ፡ ስለ ፡ አንድነት ፣ ሀገርና ፡ ወገንን ፡ ከችጋር ፡ ማዳን ፣ በመቶው ፡ ሺ ፡ በሚቆጠር ፡ በየቦታው ፡ የታሠሩትን ፡ ታጋይ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ማስፈታት ፣ የቅንጅት ፡ ግዜያዊ ፡ ችግር ፡ ከተመራጭ ፡ አጋሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ አስተካክለው ፡ ለተተኪው ፡ ትውልድ ፡ ለማወራረስ ፡ ነው ። እናም ፡ ውሃና ፡ ዘይትን ፡ ማዋኃድ ፡ ስለማይቻል ፡ የተበከለውን ፡ ዘይት ፡ ጨልፈው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ውሃውን ፡ እንዲጠቀምበት ፡ የቀየሱትን ፡ ክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውልን ፡ ጤናውን ፡ ለግሦ ፡ ምኞታቸውን ፡ አንዱ ፡ አምላክ ፡ ያሳካላቸው ፡ እንላለን ። ከባድ ፡ ሀላፊነት ፡ የሚሰማው ፡ የሕዝብ ፡ መሪ ፣ አገር ፡ እንዲለማና ፡ ሕዝቡ ፡ ጤናው ፡ ተጠብቆ ፡ ከድንቁርናና ፡ ከችጋር ፡ ማዳን ፡ ሌላ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ የለውም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እርሳቸው ፡ ከሕመም ፡ ጋራ ፡ እየታገሉ ፡ ጤነኞች ፡ ለመደገፍ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ቸልተኛ ፡ መሆን ፡ አይገባንም። የትግሬ ፡ ወያኔ ፡ አምባገነንና ፡ አረመኔ ፡ ነብሰ ፡ ገዳይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማስፈራራቱን ፡ ቀጥሎ ፡ በእናት ፡ አገራችን ፡ ስም ፡ የለመነውን ፡ ሀብት ፡ ለስለላ ፡ አውሎታል ። ሆኖም ፡ በስደት ፡ እንጀራ ፡ አገራችን ፡ የተሰጠንን ፡ መብት ፡ እንጠቀምበት ። በምትህት ፡ አይገድለን ። ለምንድን ፡ ነው ፡ ለመወያየት ፡ እንኳ ፡ የጐሪጥ ፡ እየተያየን ፡ የምንሄደው? ። የትግራይም ፡ ተወላጅ ፡ ንጹሕ ፡ ኢትዮጵያዊውን ፡ ወገናችንን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንወዳለን ። የትግራይና ፡ ኤርትራ ፡ አምባገነን ፡ ወራሪና ፡ አረመኔ ፡ ወያኔ ፡ ነብሰ ፡ ገዳይዎችን ፡ ግን ፡ ለይቶ ፡ መታገል ፡ አያስወቅስም። ኢትዮጵያና ፡ ሕዝቧን ፡ ለማውደም ፡ ቅጥረኞች ፡ ስለሆኑ ፡ በምናገኘው ፡ ሰላማዊ ፡ ትግለ ፡ ስልት ፡ ለመቋቋም ፡ የዜግነት ፡ ግዴታ ፡ አለብን ።

**በአምላኳ ፡ እርዳታና ፡ በልጆቿ ፡ ብርታት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሸንፋለች!! ።**

**ቅንጅት ፡ አንድ ፡ ነው ።**
**ኢትዮጵያም ፡ አንድ ፡ ናት ።**

**ከቅንጅት ፡ ድጋፍ ፡ ሰጭዎች ፣**
**ኩቤክ ፣ ካናዳ ።**

የካቲት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፳፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፤

## መግለጫ ፤

በየፊደሎች ፡ እራስጌ ፡ የሚታየው ፡ ነጥብ ፡ ለቃላቱ ፡ መጥበቂያነት ፡ የዋለ ፡ ነው ። ሐሣቡንም ፡ የተማርነው ፡ ከክቡር ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ሐዲስ ፡ ዓለማዬሁ ፡ በ"ፍቅር ፡ እስከ ፡ መቃብር" ፡ መጽሐፋቸው ፡ በገለጹት ፡ መሠረት ፡ ነው ። እርሳቸው ፡ ነጥቡን ፡ በእጃቸው ፡ እያስገቡ ፡ ከአጠናቀቁ ፡ በኋላ ፡ ለወደፊቱ ፡ ተተኪው ፡ ትውልድ ፡ እንዲስብበት ፡ በማሳሰቢያ ፡ አደራ ፡ ብለው ፡ ነበረ ። ነብሳቸውን ፡ ይማርና ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርባለን ።

12* "በላቲን ፡ አጻጻፍ ፡ ለማጥበቅ ፡ የሚፈለገው ፡ ቀለም ፡ ሁለት ፡ ሆኖ ፡ ይጻፋል ። በኛ ፡ አጻጻፍ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ሆኖ ፡ የተጻፈ ፡ አንድ ፡ ቀለም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ለዬብቻ ፡ ይነበባል ፡ እንጂ ፡ አይጠብቅም" ።

## ዋቢ ፤

1-2* ዶቸ ፡ ዋለ ፡ የጀርመን ፡ ዜና ፡ ማሰራጫ ። አማርኛው ፡ ክፍል ።
3* ዓለም ፡ አቀፋዊው ፡ መረብ ፡ ዜና ፡ ማሰራጫ ። ኢትዮ ፡ አንበሣ ።
4* አንድነት ፡ ድምፅ ፡ ዜና ፡ ማሰራጫ ።
5-6-7-8* ዓለም ፡ አቀፋዊው ፡ መረብ ፡ ዜና ፡ ማሰራጫ ። ኢትዮ ፡ አንበሣ ።
9* የሌተና ፡ ኰሎኔል ፡ መንግሥቱ ፡ ኃይለማርያም ፡ ትዝታዎች ።
  ገጽ ፡ 16-17
10* ሰምና ፡ ወርቅ ፤ ፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ ፭/፯ የካቲት ፲፱፻፹፩
  ድርቅና ፡ ጠኔ ፡ በኢትዮጵያ ። ገጽ ፡ 34-35
11* ዓለም ፡ አቀፋዊው ፡ መረብ ፡ ዜና ፡ ማሰራጫ ። ደብተራው ።
  በመምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ።
12* ፍቅር ፡ እስከ ፡ መቃብር ። ከሐዲስ ፡ ዓለማዬሁ ።
  ገጽ ፡ 9